# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ... 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ... 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ... 6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ... 6

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ... 7

እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... 7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 7

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ... 8

እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... 8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 8

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ... 9

ሁኔታ አዝማሚያ ... 9

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 10

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 11

# እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


በኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከሞላ ጎደል ተጠናክረው በመቀጠላቸው ምክንያት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ ቢሆንም፤ በየጣልቃው ፀሃያማ ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በፀሐይ ሀይል እየታገዙ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በአንዳንድ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የሰሜን-ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አሥር ቀናት በትግራይ፤ በአማራ፤ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ በአብዛኛው ኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤በጋምቤላ፤ በደቡብ አፋር፤ በድሬዳዋ፤ በሰሜን ሶማሌ እንዲሁም በሐረሪ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ውስጥ ከ 30 እስከ 109 ሚ.ሜ ከባድ ዝናብ በብዙ ጣቢዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአልጌ 40.0፣ በአርጆ 46.6 እና 40.2፣ በአሶሳ 42.3፣ በባቲ 52.0፣ በቻግኒ 63.2፣ በጨፋ 53.1፣ በኮምቦልቻ 45.0፣ በድሬዳዋ 98.7፣ በደባርቅ 58.8፣ በኢጃጂ 47.2፣ በጋምቤላ 109.0፣ በጎንደር 42.7፣ በላሊበላ 65.4፣ በምራብ አባያ 66.0፣ በማጂቴ 59.9፣ በማሻ 40.2፣ በነጆ 47.1፣ በኑራኤራ 45.1፣ በሾላ ገበያ 50.0፣ በስሪንቃ 62.5 እና 51.4፣ በሻውራ 54.3፣ በወረኢሉ 59.9፣ በላሬ 50.5፣ በጊዳአያና 68.7፣ በጉንዶ መስቀል 52.8 እንዲሁም በዳሊፋጊ 48.2 በሚ.ሜ የገኙባቸዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ፤ በአማራ፤ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ አፋር፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብ ሐረርጌ እና በሲቲ ዞኖች ላይ ከ25-172 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በፋፈን፣ በምስራቅ ሐረርጌ፣ በባሌ፣ በጉጂና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች አንዳንድ ቦታዎች ላይም ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 2 (ሁለት) ላነሱ ቀናት ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ ከዋግህምራና ከምስራቅ ጎጃም ጥቂት ቦታዎች በስተቀር በተቀሩት የአማራ ክልል ዞኖች፣ በአብዛኛው በአፋር፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በጋምቤላ ሁሉም ዞኖች፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩና ምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ፣ በቡኖ በደሌ፣ በምዕራብና ሰሜን ሸዋ (04)፣ በባሌ፣ በጉጂ፣ በምዕራብ ጉጂና በቦረና አብዛኛዉ ቦታዎች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በከፋና ምዕራብ ኦሞ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝዝቦች ክልል እና ሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በምዕራብ አርሲና በአርሲ፣ በኢሉአባቦራ፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በባሌና በፋፈን ዞኖች ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1    እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2      ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





የወቅቱን ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ ከእርጥበታማ (Moist condition) እስከ እጅግ በጣም እርጥበታማነት (Supper Moist) የደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፣ አስቀድመው ለተዘሩም ሆነ በዘር ላይ ለሚገኙ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ነበረው:: በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የአርብቶ አደሮችና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተገኘዉ እርጥበት ለሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎለበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር በጎ ጎን ነበረው፡፡ በአንጻሩ ተጠናክሮ ከነበረው የሚቲዎሮሎጂ ገጽታ አንጻር በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ የጎርፍ ክስተት እንዲኖር ያደረገ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከነበረው ተከታታይ ዝናባማ ቀናት ጋር ተያይዞ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በማሳዎች ላይ የውሃ የመተኛት ክስተት ተስተውሏል (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከኦገስት 11-20/2022 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ አብዛኛውን የሀገሪቱ ዋና ዋና የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶችን ያዳረሰ እና የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ተስተዎሎባቸው ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ተከዜ፣ ስምጥሸለቆ፣ ባሮአኮቦ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ተስተውሎባቸው ነበር፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት ላይኛው ዋቢሸበሌ፣ በመካከለኛው ገናሌዳዋና በጥቂት የታችኛው ስምጥ ሸለቆና እንዲሁም በታችኛው አዋሽ ኪስ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በተቀሩት በአብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ ገናሌ ዳዋ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛው ሁኔታ የክረምት ዝናብ ከሰሜን ኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ከኦገስት መጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ጀምሮ ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የሚያሣይበት ጊዜ ሲሆን፤ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ ደግሞ እየተስፋፋ ይሄዳል። በአሁኑ ጊዜ እየታዩ ያሉትና በመጪዎች አሥራ አንድ ቀናት ውስጥ የተተነበዩት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የክረምት ዝናብ ከሞላ ጎደል በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ በመካከከለኛውና በምዕራብ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል። ከዚህም በተጨማሪ በየጣልቃው በሚኖረው ጠንካራ የፀሐይ ሀይል በመታገዝ ከሚፈጠረው የደመና ክምችት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅዖ ሊያደርግ እንደሚችል ይጠበቃል።

በዚህም መሠረት በመጪዎቹ አሥራ አንድ ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ የጅማ፣ የኢሉባቦርና አርሲ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፤ ሰሜን ሸዋ፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ የባህር ዳር ዙሪያ፤ አገው አዊ፤ ሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛው ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ፤ የስልጤ፣ የወላይታ፤ የዳዉሮ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ የከፋና ሸካ እንዲሁም የሀላባ ልዩ ወረዳ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪም የምሥራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ሁሉም የአፋር ክልል ዞኖች፣ ድሬዳዋና ሀረሪ፣ ከሶማሌ ክልል የፋፈን እና ሲቲ፣ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ እንዲሁም የባሌ ዞን፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የደቡብ ኦሞ፣ ቤንች ማጂ፣ ጎፋና ጋሞ፣ ጌድኦና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በጸሀይ ሃይል ከሚፈጠሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ነጎድጓዳማ ዝናብ የሚኖርና ሲሆንና በጥቂት ስፍራዎች ላይ ደግሞ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁላይ ወር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት የዕርጥበት ሁኔታው ከሰሜን ኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የሚያሣይበት ጊዜ ሲሆን፤ በአንፃሩ ደግሞ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ አንጻራዊ መስፋፋት የሚስተዋልበት ወቅት ነው። ከግብርና እንቅስቃሴ አንጻርም በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ የመኸር ሰብሎችን የመከታተልና በተሟላ መልኩ እንዲያድጉ የሚያስችሉ የእንክብካቤ ስራዎች በስፋት የሚሰሩበት ጊዜ ነው።

በተሰጠው የአስራ አንድ ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት የእርጥበት ሁኔታው ከሞላ ጎደል ካለፉት ቀናት ጋር ተመሳሳይነት ባለው መልኩ እንደሚቀጥል የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አለፎ ባሉት ቀናትም ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች ጋር ተያየዞ እንዳንድ አካባቢዎች ከባድ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል ተጠቁሟል። በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበት በበቂ ሁኔታ እንዲኖርና የተለያዩ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች እንዲሁም የጓሮ አትክልቶች በየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ በሀገራዊው የአረንጓዴ ልማት ዕቅድ መሰረት የተተከሉ ችግኞች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የሚያስችል ሲሆን፤ በአንፃሩ ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ የጎርፍም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በቀጣይነት ከሚጠበቀው እርጥበት ጋር ተያይዞ የአረም መስፋፋትም ሆነ የተለያዩ የሰብል በሽታዎች እንዲከሰቱ የሚያስችሉ የሚቲዎሮሎጂ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችል አሰፈላጊው ቅድመ ጥንቃቄ እና ክትትል ከወዲሁ እንዲደረግ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ይመከራል። በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እርጥበት የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን፣ የግጦሽ ሳር ልምላሜን እንዲሁም የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ የውኃ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር በጎ ጎን እንደሚኖረው የሚጠበቅ በመሆኑ፤ የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቁትን የሚቲዎሮሎጂ ምቹ ሁኔታዎች ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከወዲሁ እንዲያከናውኑ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎች አሥራ አንድ ቀናት የተተነበዩት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የክረምት እርጥበት ከሞላ ጎደል በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ በመካከከለኛውና በምዕራብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት ሊኖረዉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ተከዜ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከበጣም ከፍተኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአብዛኛው አፋርደናከል፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ እንዲሁም ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ በታችኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ እንዲሁም በባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር የሚችለው ዝናብ ከላይኛው ተፋሰሶች ጋር ከሚኖረው የወንዝ ፍሰት ጋር ተዳምሮ ጫና ስለሚኖረው የወንዝ ሙላትና ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ህብረተሰቡ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እናሳስባለን።